በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
**OFFICE OF THE PRIME MINISTER**

መጋቢት 26 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# 81ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት 81ኛ መደበኛ ስብሰባውን በቪዲዮ ኮንፍረንስ ያካሄደ ሲሆን በሁለት ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ም/ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽንን (Electronic Transaction) ለመደንገግ በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ከዚህ በፊት በወረቀት መሰረት ተደርገው ሲፈጸሙ የነበሩ የግብይት እና የመንግስት አገልግሎቶች በኤሌክትሮኒክስ መስል ህጋዊ እውቅና አግኝተው ስራ ላይ እንዲውሉ የሚደርግ እንደዚሁም የኤሌክትሮኒክ ንግድ እና የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶች የዲጂታል ኢኮኖሚው አካል መሆናቸውን መነሻ በማድረግ፤ አገራችን እነዚህን ዘርፎች የምትመራበት የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት በማስፈለጉ የኤሌክትሮኒክ ንግድ እና የኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎቶችን ማዕከል ያደረገ የኤሌክትሮኒክስ ትራንዛክሽን ረቂቅ አዋጅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ አንዳንድ ማስተካከያዎችን በማከል አዋጁ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ የተወያየው የኤካ ኮተቤ ሆስፒታልን ለማቋቋም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ነው፡፡ ሆስፒታሉ የተቀናጀ፣ ጥራቱን የጠበቀ፣ ተገሊጋይ ተኮርና ተደራሽነት ያለዉ የአዕምሮ እና የአካል ሕክምና አገልግሎቶችን አቀናጅቶ የሚሰጥ ሆስፒታል ሆኖ እንዲቋቋም ለማስቻል በጤና ሚኒስቴር የቀረበ ረቂቅ ደንብ ሲሆን ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቡ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በሥራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

//